ነሐሴ 2001 ዓ.ም

## እረ ግፉ በዛ።

እረ ግፉ በዛ መጠኑን አለፈ፣
ሕዝቡ በበሽታ በርሃብ ረገፈ።
ጥቂቶች በልጽገው አብዛኛው ደህይቶ፣
ይኸው ይሰቃያል የሚሰማው አጥቶ።
አገር ተቆረሰ ድንበር ተደፈረ፣
ዜጋም ይህን ሰምቶ ቅስሙ ተሰበረ።
ሕዝባቹን ሲሰቃይ በግፍ ሲፈናቀል፣
ይህንን እያየን እንዴት ዝም እንበል፡
እንደው ዝም ብሎ ግፈኛን ማገልገል፣
እንደው በጥላቻ ሕዝብንም መበደል፣
እንደሆነ እንወቅ የሚያስቀጣ ወንጀል።
በጥቅም ተገዝቶ በሐሰት መመስከር፣
ከጨቁዋኝ ጋር ሆኖ ንጹህንን ማሰር፣
ሕዝብ እየዘረፉ አላግባቡ መክበር፣
መታረም ያለበት አስነዋሪ ነገር።
ከሕዝብ ጎን መቆም ተገቢ ነው በእውነት፣
ህሊናን ከማድማት በመሆን አገልጋይ የፋሺስት።
እረ ግፉ በዛ መጠኑን አለፈ፣
ሕዝቡ በበሺታ በጠኔ ረገፈ ።
ይሄ ሁሉ በደል ይሄ ሁሉ ግፍ፣
እንዴት ያስቺልና ያስተኛል እንቅልፍ፣
ሀገር ሀገር ቢባል ምንድነው ትርጉሙ፣
ሀገር ስትቆረስ ሕዝቡም እያለቀ እንዳለ በቁሙ፡
ቶሎ ካልደረሰ አንድነትን ፈጥሮ ከእህት ከወንድሙ።
ታሪክ ለማስመዝገብ ለመጎናጸፍ ድል፣
የግድ ያስፈልጋል ህብረት ፈጥሮ ትግል።
በሀገር በሕዝብ ስም ንግድ የተያያዛቹሁ፣
ዕድሜ ልክ በሙሉ ሥልጣን ላይ ያላችሁ፣
ሕዝቡ ይላችሁዋል ልቦና ይስጣችሁ።
እውነቱን ካየነው ማንም ቢሆን ከቶ ጥቅምን አይጠላ፣
አስከፊ እሚሆነው እራስን ለመጥቀም ማፍረስ የሰው ገላ።
ለጥቅም ብላቹሁ ሰውን የምትጎዱ፣
በገዛ ሥራቹሁ አትቀሩም ሳታብዱ።
እረ ግፉ በዛ መጠኑን አለፈ፣
ህጻን አዛውንቱ በርሃብ ረገፈ።
ሕዝብን ንቆ ረግጦ ማፈን ማሰቃየት፣
ማንም አያስጥልም ሁዋላ ሲለይለት።
ሕዝብ በገዛ ሀገሩ ሲሰቃይ ሲበደል፣
ዝምታ አይጠቅመንም አሁን ነው መታገል፣
ስለዚህ ወገኔ ግፉን ለማስወገድ ጥሪውን ተቀበል።
የርስበርስ ንትርክ የርስበርስ ዘለፋ ጠለፋ፣
ለሚሰቃየው ሕዝብ ምንም አይሰጥ ተስፋ።

በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት እንዲሉ፣
ባዕዳን ሳይቀሩ ኢትዮጵያን ለማድከም ድጋፍ ይሰጣሉ።
መሩዋሩዋጡን ትተን ለሥልጣን ለጥቅም፣
በእውነት እየሰራን ከሕዝብ ጎን እንቁም።
ማጋነን ማንኩዋሰስ በጣም ጎጂ ነው፣
ለሕዝብ የሚጠቅመው እውነት ማቅረብ ነው።
ችግር የማይፈጥረው ለጤና የሚስማማው፣
ውጤት የሚያመጣው ድጋፍ የሚያስገኘው፣
መረጃ በማቅረብ ሕዝብን ማሳመን ነው።
ላገር የምናስብ ለሕዝብም የቆምን ፣
ጊዜው ሳይመሽብን እንድረስ ፈጥነን።
እውቁ ኢትዮጵያዊ ፕሮፌሰር መስፍን፣
እየደጋገሙ እንዳስገነዘቡን፣እንደነገሩን፣
ግፉም የሚበዛው ሲያገኝ ነው ተሸካሚውን።

ይበልጣል እውነቱ፣
ከጀርመን።
ነሐሴ 2001/August 2009/